# <u>ብሆንማ ኖሮ መሆን ኢቃተ እንጂ</u>

ሐማ ቱማ

ብሆንማ ኖሮ፣ የዚያች ጸሐይ ጌታ፣

ጨረቃን ማወጣ፣ ጠዋትና ማታ፣

ብሆንማ ኖሮ፣ ነቢይ ተከባሪ፣

ቃሉ ጠብ የማትል በሁሉ ተሰሚ

ብሆንማ ኖሮ፣ የዚያ ትውልድ ቁራጭ፣

የዚያ የተስፋዬ፣ የዳሮ የአበራሽ፣

የማርቆስ፤ ይትባረክ የሁሉ ደመላሽ፣

ከወኔው ጽናቱ፣ ቢያንስ እንኳን ተቃራጭ፣

ብሆንማ ኖሮ፣ ዲያብሎስ ለሕዝብ ጠላት፣

ለሕዝብ ግን ኢጋሩ፣ አለኝታና ኩራት፣

ብሆንማ ኖሮ ለየባንዳው ኮሶ፣

እሬትና እንቆቆ፣

ለወያኔም ምንጩ፣ ለየቀኑ ለቅሶ፣

የማይለቅ ማነቆ፣

ጨካኝና ደምሳሽ፣ ዘረኛን ማርከሻ፣

አውደልዳይ ምሁሩን፣  መድረክ የማሳጣ፣

የገንጣዩን መንጋ፣ ማመክን የማጠፋ፣

ብሆንማ ኖሮ፣ አልሆን አልኩኝ እንጂ፣

አስቸገረኝ እንጂ፣

ህሊናዬ ሲደክም፣ ሆዴ እያበጠ፣

ከርስ አምላኩ አርጎ፣ አዋረደኝ እንጂ፣

ባለጌ ዘረኛ፣ ጠባብ ትምክህተኛ፣

ታጋይ ብሎ አቃፊ፣ ግሙን ሽብርተኛ፣

አጋር ብሎ አቃፊ፣ ውድቁን ሻዕቢያ፣

ብሆንማ ኖሮ፣ ንቁ እንደዚያ ትውልድ፣

ጽኑ ኢትዮጵያዊ፣ ሀገሩን የሚወድ፣

ነገረ ሁኔታው፣ በሆነማ ሌላ፣

ወጣቱን ማስተኛት፣ በከሽፈ ሴራ፣

የማውግዘው ሁኜ፣ ማልሰማው ቢጣራ፣

ብሆንማ ኖሮ፣ ለወያኔው ፍየል፣ የነብር ቀበኛ፣

የራበው ጅብ መንጋ፣ ለፈሪ አህያ፣

ብሆንማ ኖሮ!

መሆን አልሆን ብሎ፣ ባይቸግር ባይጎዳ፣

ሆድ አደር ባይበዛ፣ ማፈሪያ ያ ባንዳ፣

ዛሬ ቢኖርማ፣ የአርበኛው ትውልድ፣ የባንዳ ማርከሻ፣፣

የየካቲት ጀግኖች፣ የጨቋኞች ጠላት፣ የውድቆች መሸኛ

ባንሆንማ ኖሮ፣ "ሰው ጠፋ እንዴ?" አስባይ፣ ያለፈውን ሰራዥ፣

የድክመት ምልዕክት፣ ኩሩን ታሪክ በራዥ፣

ብንሆንማ ኖሮ፣ የዚህ ተጻራሪ፣

ፍጹም ቆራጥ ዜጋ፣ ታሪክ አስከባሪ፣

ሀገርን አፍቃሪ፣

የድፍረት ምልዕክት፣ አርአያ መስካሪ፣

ብንሆንማ ኖሮ፣ መሆን አቃተ እንጂ፣

ለወያኔ መርዙ፣ ገዳይ አሳዳጁ፣ ምህረት አልባ አጥፊ፣

ስቃይ ምሬት ሞትን፣ በቤታቸው ከታች፣

ክፉ አሸባሪ፣

ብሆንማ ኖሮ፣ የወያኔ ምጸት፤ ገሀነም እንጦርጦስ፣

ጨራሽ ካንሰር ህመም፣ ያ ቀሳፊ በሽታ፣ የሚባለውም ኤይድስ፣

መሆን ብችልማ!

ከአልጋ  ባቆራኘው፣

ቆርጬ ቆራርጬ፣ ባስጎራው ባስጮኸው፣

የፍጹም ስቃይ ሞት፣ ባለቤት ባደርገው፣

ብረካ ብሞካሽ፣ ሰማዕት ተበቅዬ፣

ለእነ ደብተራውም፣ አልረሳሁም ብዬ፣

ብሆንማ ኖሮ፣ ደመላሽ ማኮራ፣

 ሕይወቴም ተከብሮ፣  ሞቴን የምጠራ።